# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ግንቦት 6 ቀን 2 ሺህ ዓ. ም
May 14, 2008

## በሰማዕቶቻችን ደምና አጥንት እንዲሁም በሕዝባችን ቆራጥ ተጋድሎ የተጎናፀፍነው የግንቦት ሰባት ታሪካዊ ድል እስኪመለስ ዛሬም እንደትናንቱ ሕዝባዊው ትግላችን ይቀጥላል!!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱም ለሌሎችም በአርዓያነታቸው ሲጠቀሱ የሚኖሩ አንፀባራቂና ታሪካዊ ድሎችን ሲያመዘግብ ለመኖሩ ምስክር መጥራት አያሻውም፡፡ በተለይም ከፈላጭ ቆራጩ የዘውድ ሥርዓት ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተገላገለበትን መስከረም ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስድስትን በዋናነት ስንጠቅስ የየካቲት ስልሳ ስድስቱ አብዮትም አብሮ መነሳቱ አይቀሬ ነው - አንድም ሁለትም ናቸውና፡፡ በዚሁ አንፃር ከአያሌ ታሪካዊ ቀናት እፁብ ድንቁን ግንቦት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ዓመተ ምህረትን መለስ ብለን ስናስታውስ በተለይ በዚያ ታሪካዊ ዕለት ማግሥትና በኋላ ሕይወትን ያህል ክቡር ዋጋ በመክፈል ዝንታለም ሲታወስ የሚኖር አርዓያነትን አበርክተውልን ያለፉት ሰማዕታት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንንና እህቶቻችን ከሁሉም ቀድመው ከፊታችን ድቅን ይላሉ፡፡ እኒያ ሰማዕት ወንድምና እህቶቻችን የከፈሉት የደምና የአጥንት ክቡር ዋጋ መና መቅረት የለበትምና የትግሉ አቀጣጣይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፍትሕ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ሥርዓት ምሥረታ የጀመረውን ትግል አጋግሞ ዛሬም በ"እምቢኝ ለህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ" መፈክር ቀጥሏል፡፡ ይህም ትግሉን በአቸናፊነት ለመወጣት የሕዝባችንን የማይታጠፍ ቁርጠኝነት በግልፅ አመላካች ሆኗል፡፡

ግንቦት ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት በእርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ የእኩልነትና የፍትሕ ጥማቱን ልክ በውል ያስረገጠበትና ለአዲስ ሥርዓት ምሥረታም ዝግጁነቱን በይፋ የገለፀበት ታሪካዊ ዕለት ሲሆን በኢትዮጵያ ወዳጆችና በዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ዘንድ ሳይቀር ዝንታለም ሲዘከር የሚኖር ክቡር ቀን ነው፡፡ እንደሚታወቀው በጠመንጃ ለሥልጣን የበቃው የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ እንደቀድሞው ሁሉ በግንቦት ዘጠና ሰባት ምርጫም ባሸናፊነት እንደሚወጣ ፍፁም የተሳሳተ ግምት አሳድሮ ነበር፡፡ በወቅቱ የልብ ልብ ሰጥተውት የነበሩት የምርጫ ቦርድን፥ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፥ የምርጫ ሕጉንና የሕግ አስፈፃሚ አካሉን ሁሉ ሙሉ በሙሉ በራሱ ቁጥጥር ሥር ማድረጉ

ሲሆን እኒህ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ዛሬም ስለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሲያወራ ፍፁም ሃፍረት አይሰማውም።

ግንቦት ሰባትን የራሱ ታሪካዊ የድል ቀን ለማድረግ ቆርጦ የተነሳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በዕለቱ ደከመኝና ሰለቸኝ፥ ሰልፉ ረዘመ፥ ፀሐዩ ገረረና ሌላም አንዳች ምክንያት ሳይደረድር ከጧት እስከማታ ፍፁም ጨዋነትና ትዕግሥትን በተላበሰ መንገድ ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ እንዲመሩት ለፈቀዳቸው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ወገንተኝነቱን አረጋግጧል። ለለውጥ ዝግጁነቱንም በተግባር አስመስክሯል። ይሁን እንጂ ህወሓት/ኢሕአዴግ የአደባባይ ሽንፈቱን ለመቀበል ካለመፍቀዱም በላይ "ምርጫው ነፃና ፍትሓዊ ይሆናል" እያለ ዓለማቀፉን ማኅበረሰብ ጭምር ሲያታልልበት የኖረው ድብቅ ባሕርይው ገሃድ ወጣ። ሥርዓትና አግባብ ባለው መንገድ ፍላጎቱን በድፍረት የገለጠውን የኢትዮጵያን ህዝብ ውሳኔም ለመቀልበስ በሥርዓቱ ቁንጮ በመለስ ዜናዊ ቀጭን ትዕዛዝ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ የመጀመሪያው እርምጃ ሆነ። አከታትሎም ህወሓት/ኢሕአዴግ የምርጫ ሣጥን እስከመገልበጥ በደረሰ ተራ ሌብነት ተሰማራ። "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" መፈክር አንግቦ በወጣ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ ሕፃንና ሴት ሳይለይ አሰቃቂና ዘግናኝ ጭፍጨፋውን አግዓዚ በተሰኘው ቅልብ ነፈሰ ገዳይ ጦር በመመራት የጅምላ ጭፍጨፋ አካሄደ።

በቅድመት-ግንቦትና ድኅረ-ግንቦት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት እንዲሁም በቀጣይነት እስከዛሬ በአምባገነኑና በዘረኛው የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያለማቋረጥ የሚወርደው ስቃይና መከራ በብሔራዊና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና መገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች በግልፅ ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በተለይ የግንቦት ሰባት ማግሥቱ የሥርዓቱ አረመኔያዊ እኩይ ድርጊት የሥርዓቱ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ተገዶ ባቋቋመው አጣሪ ኮሚሽንም ጭምር ገሃድ ወጥቷል። ሐፍረት ጨርሶ ያልተፈጠረበት መለስ ዜናዊ ግን አጣሪ ኮሚሽኑ የደረሰበትን ውጤት ሳይቀር ለማስለወጥ የኃይል እርምጃ ከመውሰዱም በላይ የኮሚሽኑን አባላትና ቤተሰቦች የማሰር የማንገላታትና የማሳደድ ተግባር ፈፅሟል። ከመቼውም ጊዜ በተባባሰ ሁኔታ ዛሬ የምስኪኑ ኢትዮጵያዊ የዕለት ተዕለት ዕጣ ፈንታም እሥር፥ እንግልት ሞትና ስደት ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህም ሆኖ ሰማዕት በሆኑትና በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ የተጎናፀፍነው የትናንቱ የግንቦት ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ታላቅ ታሪካዊን ድል መልሶ ለመጎናፀፍ ዛሬም እንደትናንቱ ከተባበረ ሕዝባዊ ትግል ውጭ አማራጭ የለም። **የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ)** በግንቦት ሰባት ማግሥት ከሕዝባችን እጅ ህወሓት/ኢሕአዴግ በጠመንጃ አፈሙዝ የነጠቃቸው ድሎች እስኪመለሱ ትግሉን

ይቀጥላል፤ ከሌሎች የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋርም በጋራ ትግሉን ያፋፍማል። **ኢሕአፓ** (ዴ) ሕዝባችን መልሶ የድሉ ባለቤት እንዲሆን የሃገር ሉዓላዊነትን፥ የሕዝብ አንድነትንና የማናቸውም ሰብዓዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ መከበርን መሠረት ያደረገ ሕብረት መፈጠርን ወሳኝነትም አጥብቆ ያምናል። ለዚህም ተግባራዊነትና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል መሣሪያ ሆኖ ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን ዳግም ሊያረጋግጥ ይወዳል።

በግንቦት ሰባት ማግሥት የተነጠቁ የሕዝባችንን ድሎች ለማስመለስ በሕብረት እንነሳ!
ግንቦት ሰባት ዘጠና ሰባት ለዘለዓለም ሲዘከር የሚኖር ታሪካዊ የድል ቀናችን ነው!
ያለጥርጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!

**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Siver Spring , MD 20910**

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Fax: 202-449-8363**
**Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**